Summer RISE
Connecting Students to Careers

# ሠመር ራይዝ (Summer RISE) 2023 የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት

Department of Partnerships
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
850 Hungerford Drive, Room 159, Rockville, Maryland 20850

## የወላጅ፣ ሞግዚት፣ ብቁ ተማሪ ስምምነት

ይህ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙ 11ኛ ክፍል ለሚገቡ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በሠመር ወቅት የሙያ ሥራ ልምዶችን ለመቃኘት እንዲያስችላቸው ነው።

1. **ተረድተው ተስማምተዋል** እርስዎ ወላጅ/አሳዳጊ እንደመሆንዎ መጠን፥ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) 11ኛ ክፍል ወይም 12ኛ ክፍል የሚመዘገብ/የምትመዘገብ ተማሪ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ ፈቃደኛ መሆንዎን 2023 –2024 የትምህርት ዘመን።
2. **ተገንዝበው ተስማምተዋል** ተማሪው(ዋ) በቀን 8 ሰአት ያልበለጠ፣ በሳምንት 30 ሰአት ያልበለጠ የሚፈለገውን 10 ሰአት ለመሥራት በተመደበ(ች)በት ቢዝነስ፣ ድርጅት፣ ኤጀንሲ ወይም አካል ("የሙያ ልምድ አስተናጋጅ") ጣቢያ የሙያ ልምድ **ለመቅሰም 5 ሳምንታት እና በአጠቃላይ እስከ 50 ሰአት ድረስ በሙያ ላይ የተመሰረተ የመማር እድል ላይ እንደሚሳተፍ/እንደምትሳተፍ** የሥራ ልምድ ጁን 26, 2023 ጀምሮ እስከ ጁላይ 28, 2023 በሳምንት እስከ አምስት ቀናት፣ በአምስት ሳምንታት ሊጠናቀቅ ይችላል። Summer RISE ተሣታፊዎች ከሰኞ እስከ ዓርብ 8:00 AM በፊት አይጀምሩም፥ ወይም 6:00 PM ካለፈ በኋላ ሥራ ላይ አይቆዩም። ተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ አበል ለማግኘት በሙያዊ ክህሎት እና በፋይናንስ ትምህርት አውደ ጥናት ላይ 50 ሰአት መሳተፍ እና ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። ከሙያ ልምድ ሰጪ አካል የሚመለከተው ባልደረባ ("Career Experience Host Designee(s)") የሠመር ራይዝ ፕሮግራም " Summer RISE Program" ሲጠናቀቅ ተቀባይነት ያለው 50-ሠዓት የሙያ ልምምድ ማረጋገጫ ይሰጣል።
3. **ተስማምቻለሁ** Summer RISE Program ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች በቅድሚያ በአካል ወይም ቨርቹወል ሙያዊ ክህሎት እና በፋይናንስ እውቀት አውደጥናት መከታተል እንዳለባቸው ተገንዝቤአለሁ። አውደ ጥናቱ የሚካሄደው ከሚፈለገው የፕሮግራም ሰአት በተጨማሪ ነው።
4. **ገብቶኝ ተስማምቻለሁ** "Summer RISE Program" በአካል የሚሳተፉ ተሳታፊዎች ከያሉበት ቦታ የሙያ ልምምድ ወደሚያገኙበት ሥፍራ ለመመላለስ የመጓጓዣ አቅርቦት የራሳቸው ሃላፊነት መሆኑን "Youth Cruiser SmarTrip® Cards" በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ይገኛል።
5. **በመገንዘብ ተስማምተዋል** በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) Summer RISE ፕሮግራም ሠራተኞች ለተመዘገቡት ተማሪዎች በሙሉ ሙያዊ ትምህርት ልምምድ/Career Experience ለመስጠት የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ፣ የሆነ ሆኖ Career Experiences የቦታ መገኘትን መሠረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል። "Summer RISE Program" ሠራተኞች ተሳታፊ ተማሪዎችን በጅኦግራፊያዊ አመቺነት፣ በአካል እና/ወይም ቨርቹወል እንደአመቺነቱ ከተገኘ ኢንዱስትሪ ጋር ለማቀናጀት ይሞከራል።
6. **በመገንዘብ ተስማምተዋል** የሠመር ራይዝ ፕሮግራም-ስንክልና ያላቸው ግለሰቦች የትምህርት ደምብ "Individuals with Disabilities Education Act (IDEA)" እና በተጓዳኝ የሜሪላንድ ህግ መስፈርት በሚፈለጉት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ዉስጥ አልተካተተም።
7. **በመገንዘብ ስምምነት ተደርጓል**የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች የራሳቸውን መርኃግብር በቀጥታ Career Experience Host Designee(s) ጋር የማስተባበር ሃላፊነት እንዳላቸው የሙያ ልምምድ ሠዓቶች ከሰኞ እስከ ዓርብ 8:00 AM እስከ 6:00 PM ብቻ ይሆናል።
8. **በመገንዘብ ተስማምቻለሁ** "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች ጥሩ ክትትል የማድረግ ልምድ፣ ስነምግባር፣ ትክክለኛነት፣ ስነስርአት መጠበቅ፣ ሳይዘገይ ወዲያውኑ ማድረግ፣ ብስለት፣ ተገቢነት ያለው አለባበስ፣ አግባብ የሆነ የቢዝነስ ስነ-ምግባር፣ ማሳየት እንደሚጠበቅባቸው እና ቨርችወል የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ከሆነ፣ እንደሚታወቀው በቪድኦ እንደሚሆን የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች በሙያ ልምድ አሳታፊዎች የማይፈታ ጉዳይ ካጋጠማቸው ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤት "Summer RISE program office" በኢሜይል summer-rise@mcpsmd.orgወይም በስልክ ቁጥር 240-740-5599 በመደወል ማሳወቅ አለባቸው።
9. **ተስማምቻለሁ**በሠመር ራይዝ ወቅት ለተማሪ ድጋፍ ለመስጠት እና ጥያቄዎች ሲኖሩ ለመፍታት የሠመር ራይዝ አስተማሪ ተባባሪ እንደሚመደብ በመገንዘብ አንድ ተማሪ በአካል በሚደረግ የስራ ልምምድ ለመሳተፍ ከመረጠ(ች)፣ የሠመር ራይዝ መምህር ተባባሪ ወይም የሰመር ራይዝ ሰራተኞች የተማሪው(ዋ)ን የሥራ ልምምድ በርቀት የመቆጣጠር አማራጭ ይኖራቸዋል።
10. **በመገንዘብ ተስማምተዋል**የስራ ልምምድ የሚሰጡ አካላት የማጣራት እና/ወይም ክትባቶችን የመሣሰሉ ተጨማሪ መስፈርቶች ሊኖራቸው እንደሚችል ጁን 26, 2023 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከሚጀምርበት ቀን በፊት ማንኛውንም ተጨማሪ መስፈርቶችን ለማሟላት ከስራ ልምድ አስተናጋጅ/ተወካይ ጋር በቀጥታ መስራት የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ሃላፊነት ነው። አንድ ተማሪ የአስተናጋጁን መስፈርቶች ማሟላት ካልቻለ(ች)፣ ከተገኘ ሌላ እድል ይሰጠዋል/ይሰጣታል።
11. **ስምምነት ተደርጓል** ወላጅ/አሳዳጊ እና የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች በኮቪድ-19 ወቅት የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከል (CDC) መሰረታዊ መመሪያዎችን መገንዘባቸውን እና መረዳታቸውን ገልጸዋል፣ ይህም በሚከተለው በይነመረብ ላይ ይገኛል:- https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/guidance-business-response.html#more-changes ተማሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ የመከላከል ዘዴ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ወላጅ/አሳዳጊ ተማሪያቸው ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዙ ገደቦች ምክንያት በአካል በመገኘት የሥራ ልምምድ ላይ ለመሳተፍ ከመረጡ በራሳቸው ፈቃደኝነት እንደሚያደርጉት ተገንዝበዋል፥ ይህ ስምምነት በስራ ቦታ እና ከኮቪድ-19 ጋር የተዛመዱ የፕሮቶኮል መስፈርቶችን የሚመለከት መሆኑን አውቀዋል። የኮቪድ-19 ተጋላጭነት ለሚያጋጥመው/ለሚያጋጥማት ተማሪ MCPS ምንም አይነት ሃላፊነት አይወስድም።

12. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ክፍያ ለማግኘት ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ልምዳቸው መካከለኛ ነጥብ እና የፕሮግራም መጨረሻ ዳሰሳ እንደሚያጠናቅቁ በመገንዘብ ተስማምተዋል  የባጀት/ፈንድ ድጋፍ የሚገኝ ከሆነ።

13. በመገንዘብ ተስማምተዋልየሙያ ዝንባሌ እና ችሎታን ከዝንባሌአቸው ጋር ለማመሣከር እንዲያመች የተማሪው(ዋ) መረጃ ለሙያ ልምድ ሰጪ/ተወካይ ይሰጣል። የሙያ ልምምድ ሰጪ/ተወካይ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎችን መረጃ የሚያገኙት እንደዝንባሌአቸው ለመመደብ እና/ወይም ከማን ጋር እንደሚቀናጁ ለማወቅ ስለሚረዳ ነው። ከሰመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በሙሉ በሙያ ልምድ አስተናጋጅ ወይም ተወካይ በኩል ለማንኛውም ሶስተኛ ወገን እንደማያጋሩ በመገንዘብ ተስማምተዋል።

14. በመገንዘብ ተስማምተዋል የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ ፈንድ ከተገኘ ለፕሮግራም ወጪያቸው እንደ ማካካሻ የሚቆጠር አበል እንደሚያገኙ ተስማምተዋል። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሥራ ልምምድ ሲጠናቀቅ ለተማሪው(ዋ) ድጎማ የሚከፈለውን ቼክ MCPS አካውንቱን ለሚያስተዳድረው ባንክ የተማሪውን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስም እና የቤት አድራሻ ይሰጣል። MCPS የተማሪውን የቤት አድራሻ ፈንዱን ለሚያስተዳድረው ባንክ እንደ አማራጭ ለመስጠት ከፈለገ(ች) ቼኩን ከ Department of Partnerships office ለመውሰድ ወደዚያ ቢሮ እንዲላክ ሊጠይቅ ይችላል። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ወይም ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ስለ ተማሪ አበል ክፍያ ጥያቄ ካላቸው summer-rise@mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤትን "Summer RISE Program office" መጠየቅ ይችላሉ።

15. በመረዳት ተስማምተዋልየሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ፕሮግራሙ በሚጠናቀቅበት ጊዜ በሙያ ልምድ ሰጪዎች ዘንድ ሥራ ለመቀጠር የይገባኛል ጥያቄ ስለማይኖር እንደሠራተኛ ለመቀጠር ተስፋ ማድረግ እንደሌለባቸው

16. በመገንዘብ ተስማምተዋልየሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሣታፊዎች የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ሙያዊ ትምህርት ልምምድ በሚያገኙበት ቦታ ተቀጣሪዎች ሊሆኑ እንደማይችሉ የሙያ ልምድ ሰጪዎች ከሠመር ራይዝ ተሳታፊዎች የሥራ እንቅስቃሴ ምንም አይነት የራሳቸውን ጥቅም አይወስዱም፣አንዳንድ ጊዜ እንደውም ሥራቸው ሊስተጓጎል ይችላል። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች በ "Career Experience Hosts" ሥራ ላይ በመደበኛነት እንደማይሠሩ፣ ወይም በዘወትር ሥራቸው (ለምሳሌ:- ፋይል ማድረግ፣ ሌላ የጽህፈት ሥራቸውን መሥራት፣ ወይም ደንበኞቻቸውን ማስተናገድ) ላይ ጣልቃ እንደማይገቡ ግንዛቤ በማግኘት ተስማምተዋል። የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪዎች ለተማሪዎች  ስለ ቢዝነሱ/ስለ ድርጅቱ እና በሥራ ድርሻቸው ላይ የሚያተኩሩ ኃላፊነቶች፣ እና ስለ ቢዝነሱ/የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሚመለከት ለተማሪዎች ሁሉ አቀፍ ግንዛቤ ይሰጧቸዋል። ተማሪው(ዋ)/ተማሪዎቹ እነዚህን ሥራዎች በመሥራት ጥራትን፣ ሙያን፣ እና ሥራ አስኪያጅ ወይም ማናጀር ውጤታማ ሆኖ የሚሠራበትን አሠራር እና በበርካታ የሥራ ቀጣሪ ድርጅቶች አካባቢ ለመጠቀም የሚያስችል ጠለቅ ያለ መረዳት/እውቀት ያገኛሉ።

17. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊ ይህን የስምምነት ውል፣ በሙያ ልምድ አስተናጋጆች የተሰጡትን ደንቦች እና መመሪያዎች፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም የተሰጡትን ደንቦች ካላከበረ(ች)  MCPS በሚወስነው መሠረት፣የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሊቋረጥ የሚችል ሲሆን የአበል ድጎማውንም ለማግኘት ብቁ አይሆንም/አትሆንም።

18. በመገንዘብ ተስማምተዋልእርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን፥ ለተማሪ የሠመር ራይዝ የሥራ ልምድ ሰጪው ተቋም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድርጅት አለመሆኑን  እንደነዚህ ዓይነት ድርጅቶች የሙያ ሥራ ልምምድ እንዲሰጡ (Career Experience Hosts) የሚመረጡት እነርሱ ለተማሪዎች የሚሰጡት የሙያ ልምድ የሚሻልና ተመራጭ ዕድል በመሆኑ፥  እና የሙያ ልምድ ሰጪዎቹ ህጉን፥ የትምህርት ቦርድን ፖሊሲዎች፥ እና የ MCPS ደምቦችን የሚያከብሩ መሆናቸውን መሠረት በማድረግ ነው። ነገር ግን፥ MCPS እና/ወይም የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሠራተኛ የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪውን እና ወይም የወከለውን ተቋም አይቆጣጠሩትም።

19. በመረዳት ተስማምተዋል እርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን ተማሪው(ዋ) በሠመር ራይዝ ፕሮግራም  ከመሣተፉ(ፏ) ጋር በተገናኘ ምክንያት ምንም አይነት ተጠያቂነት ወይም ብልሽት ቢያጋጥም MCPS ተጠያቂ እንደማይሆን

## ተጨማሪ ስምምነት

ተማሪ ኦንላይን ሲመዘገብ-ስትመዘገብ፣ ወላጅ/ሞግዚት የሚከተሉትን የተስማሙ መሆናቸውን ተማሪው(ዋ) ማረጋገጫ ይሰጣል/ትሰጣለች:-

- ❏ ተማሪው(ዋ) በሚሣተፍበት-በምትሣተፍበት ወቅት ቪድኦ ለመቀረጽ፣ ፎተግራፍ ለመነሣት፣ እና/ወይም ሪኮርድ እንዲደረግ/እንድትደረግ ተፈቅዷል። እነዚህ ምስሎች እና/ወይም ሪኮርድ የተደረጉ ነገሮች ስለ ሠመር ራይዝ ማስተዋወቅን ጨምሮ ምስሎቹን ለመጠቀም መጠየቅ ሳያስፈልግ ለተለያየ ዓላማ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።  በዚህ መልክ ጠቀሜታ ላይ በመዋላቸው ተማሪው(ዋ) ምንም ካሣ አይከፈለውም/አይከፈላትም እና MCPS ሁሉንም ምስሎች፣ ቪድዮዎች፣ እና የተቀረጹ/የተቀዱ ነገሮችን እና ሪኮርድ የተደረጉ ወይም የተወሰዱ ሥራዎችን የመጠቀም መብት አለው።
- ❏ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ባልደረባ ወይም የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪ ተቋምን የሚወክል አካል ተማሪው(ዋ) በሠመር ራይዝ ምዝገባ ወቅት የሰጠ(ች)ውን MCPS ያልሆነ ኢሜይል አድራሻ በመጠቀም ለተማሪው(ዋ) ኢሜል ሊያደርጉ ይችላሉ። ያለፈቃድ/ያለስምምነት ከሶስተኛ ወገን ወደ MCPS የተማሪ ኢሜይል አካውንት ኢሜይሎችን ለመላክ ስለማይቻል ተማሪው(ዋ) መሳተፍ አይችልም/አትችልም። ከሙያ አስተናጋጅ/ተወካይ የሚመጡ የኢሜይል መልእክቶች የሚገናኙት ከሠመር ራይዝ ጉዳዮች ጋር ብቻ ነው።
- ❏ MCPS የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሰራተኞች ወይም የስራ ልምድ አስተናጋጅ ተወካይ ለተማሪው(ዋ) በሰመር ራይዝ የተማሪ መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ከሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮችን ብቻ ከተማሪው(ዋ) በተሰጠው ስልክ ቁጥር በመጠቀም ሊደውሉለ(ላ)ት ወይም መልክት ለመላክ ይችላሉ።
- ❏ የሠመር ራይዝ ተማሪ በግል ወይም በስራ ተሽከርካሪ የሞያ ልምምድ አስተናጋጅ ተወካይ ወይም ከሠመር ራይዝ ሰራተኞች ጋር ከስራ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች በሚነዱ ተሽከርካሪዎች እንዲሣፈር/እንድትሳፈር ተፈቅዶለ(ላ)ታል፣ እናም በዚህ ምክንያት ለሚፈጠር ማንኛውም ጉዳት MCPS ተጠያቂ እንደማይሆን ተማሪ እና ወላጅ/አሳዳጊ በመመገንዘብ ተስማምተዋል።

## ፊርማ

በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ለመሣተፍ የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት መኖሩን ለማረጋገጥ የሠመር ራይዝ ተማሪ የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ ይፈርማል/ትፈርማለች። በምዝገባ ወቅት፣ ጁን እና ጁላይ 2023 ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም ማግኘት የሚቻልበት የወላጅ/አሳዳጊ ስም፣ ስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ ያስፈልጋል።